የሰ/መ/ቁ.19142

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

3. አቶ አሰግድ ጋሻው

4. ወ/ት ሒሩት መለሰ

5. አቶ አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ መላኩ ማሞ

**ተጠሪዎች፡-** እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ (3 ሰዎች)

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ከስረ-ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የማቅረብ መብትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የጀመረው በሰ/ሸዋ መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከአክስታቸው በውርስ የተላለፈላቸው ቤት የአሁኑ አመልካች ለብቻው ይዞ ሊያካፍላቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን እንዲያካፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቹ በሰጡት መልስ የኑዛዜ ወራሽነታቸውን ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት አረጋግጠው የጨረሱ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብ እንደማይገባው ክሱም ቢሆን በይርጋ የሚቋረጥ በሆኑት እንዲሁም የቤቱ ግምት የተጋነነ መሆኑን በመግለጽ ተከራክርዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ኑዛዜው በህጉ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አያሟላም ክሱም በይርጋ አይቋረጥም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ ቤቱ በባለሙያ እንዲገመት ትእዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ላይ አመልካች ለአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪዎችን ሳይጠራ የይግባኝ ቅሬታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 መሰረት ዘግቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ኑዛዜው መፍረሱ እና የይርጋው መቃወሚያም ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅረበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ምርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪዎች ላቀረቡት ክስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያዎቹን ውድቅ በማድረግ ቤቱ እንዲገመት ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በስረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ገና አልሰጠም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320(3) መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ሲሰጥ ከስረ-ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማለት እንደማይፈቀድ እና ይግባኝ ማለት የሚቻለው የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ የመሰለውን ብይን ከሰጠ በኋላ በስረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልሰጠ መሆኑ ከፍ ሲል በተጠቀሰው የስ/ስርአት ህግ መሰረት በብይኑ ላይ ይግባኝ ሊልበት እይችልም፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ላይ ያላቸውን ቅሬታ ይግባኝ ሊያቀርቡበት የሚችሉት ፍ/ቤቱ በስረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ የቀረበው ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ የስ/ስርአት ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ

ይግባኝ የማይባልበት መሆኑን ገልጾ አቤቱታውን ውድቅ ከማድረግ ፋንታ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መዝጋቱ ተገቢ አልነበረም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በስረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ በመቃወሚያው ላይ ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ አይችልም፡፡
2. የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 190/97 መጋቢት 06/1997 ዓ.ም ይግባኙ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 በመዝጋት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ